# አገርንና ሕዝብን ከጥፋት መልእክተኞች ማዳን የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው

በአለም የተበተናችሁ ትውልደ ኢትዮጵያዊያንና በአገር ቤት ያላችሁ ኢትዮጵያዊያን፣ የሲኖዶስ የደብር አለቃዎች፣ ካህናት፣ መዘምራን፣ የሰንበት ተማሪዎች፣ የአገሪቱ ብ/ብ/ሰቦች፣አርሶ አደሩ፣ ለንግዱ ማህበረሰብ ፣ለፓርላማ አባላት፣ ለፖሊስና ለመከላከያ ሠራዊት፣ ለደህንነት አባሎች በሙሉ፤

እናት አገራችን ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ የብዙ ታሪክ፣ የሐይማኖት፣ የብሔር ብሔረሰቦች መናኸሪያ፣ የቅርስ ባለ ቤት በመሆን በብሉያት፣ በአዲሳት፣ በታሪክ ፀሐፊዎች የተመዘገበችና የጥቁር አገር መኩሪያ የሆነችው እናት ኢትዮጵ ያ በአሁኑ ጊዜ ያለችበትን ሁኔታ አዲሱን ትውልድ አንገት የሚያስደፋ፣ ለትውልዱ የታሪክ ጠባሳን ገዢዎቻችንና የሃይ ማኖት መሪዎች ነን ባዮች እያስቀመጡልን ይገኛሉ።

የውጭ ሲኖዲዮስ፣ የአገር ቤት ሲኖዶስ ፣የክልል መንግስታት በማለት በጎሣ፣ በመንደርና በጎጥ ልጅነት፣ በአቻ አምቻ ጋብቻ፣ በቤተክህነቱም በመንግስቱም በጎጥ ተደራጅተን በመጠፋፋት ላይ እንገኛለን።

እንደባለፉት አባቶች እንደነ አቡነ ጴጥሮስ፣ እንደግብፃዊው አቡነ ስምኦን፣ እንደነ አቡነ ማቴዎስ በአገራችን እንደነ አ ቡነ ሚካኤል የሚመክርና የሚያስታርቅ አባት በማጣታችን አገርንና ሕዝብን በከዱ አምባገነኖች ታጥረን እንገኛለን። 3000 አመት ታሪክ ያስመዘገበችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስያን በእነዚህ የስልጣን ጥመኞችና ዘረኞች የተነሳ መሠረቷና እምነቷን ታሪኳና አንድነቷ እየተናጋ ይገኛል።
በተለይ በአውሮፓና በአሜሪካ ያለው መተረማመስ ለዚህ ምስክር ይሆናል። በስደት ላይ ያለው ኢትዮጵያዊ ለአገሩና ለ ተተኪው ትውልድ ጥቁር አሻራ እያስቀመጥንለት መሆኑ ይህ አዲሱ ትውልድ የተረዳው አይመስለኝም።
በአለም የተበተነው ኢትዮጵያዊ በያለበት ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የታነፁ ቢሆንም ቅሉ ለተተኪው ትውልድ እያስተ ላለፍን ያለነው አገሪቷም ተበትና ሕዝቡም በጎጥ ተለያይቶ እንዲኖር እየተደረገ እንጂ አንድነት፣ ፍቅርንና ሠላምን የ ሚያመጡልን መንገድ እየተከተልን ያለመሆናችንን ሁላችንም ልንገነዘብ ይገባናል።
ቤተክርስቲያን የምታስተምረው ሠላምን፣ ፍቅርን፣ አንድነትንና ይቅር መባባልን ሆኖ ሳለ ዘመናዊ መሰል ካድሬዎች ዘረ ኝነትን፣ ጎጠኝነትንና ራስ ወዳድነትን በማስፋፋት ከክርስቶስ ልጅነት ሕዝቡን እያለያዩት ይገኛሉ።
በዚህ የቤተክርስ-ቲያን ቀኖና መፍረስ ምክንያት የቤተክርስቲያን ሕግ ይከበር ማለትም እንደወንጀል ተቆጥሮ ፈሪሀ ክር ስቶስ ቀርቶ በምትኩ አድርባይነትና ራስ ወዳድነት ሰፍኖ ይታያል። የስደት ኑሮ ያልገባውና ማኅበረሰባዊ ችግሮችን በው ይይት መፍታትና ይቅር መባባልን የተሣናቸው የሃይማኖት አባቶች፣ ትውልዱና ሕዝቡ በዚህ ቀኖና መፍረስ በነፍስም - በስጋም ያስጠይቀናል።

## በኢትዮጵያ የፓትርያርክ አሿሿምና አመጣጥ

ከዚህ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የፓትሪያርክ አመጣጥና መሠረት ከውጭ ከእስክንድርያ፣ ከሶሪያ እየተላኩ የመጡ አባቶች እንደነበሩ ይታወቃል። የመጀመሪያው አባታችንም ከፍሬምናጦስ ቀጥሎ በ911 ዓ.ም አቡነ ጴ ጥሮስ የተባሉ ጳጳስ ተላኩልን፤ በዚህ ጊዜ ሁለቱ መነኮሳት ከእስክንድሪያ የተላኩ አስመስለው አቡነ ጴጥሮስ በቀኖና ያልተሾሙ መሆኑን አቅርበው አቡነ ጴጥሮስ ታሠሩ፤ ይህን ተንኮል የጠነሰሰው አቢዶ ጳጳስ ሆነ።
እርሱም ወርቅና ብር ሠርቆና ዘርፎ ወደ አገሩ ተመለሰ። በዚህ ጊዜ የመንግስቱ መቀመጫ ከአክሱም ወደ ላስታ በ933 ዓ.ም ተዛወረ።
በዚያን ዘመን ጃንስዩም ለእስክንድሪያ ሲኖዶስ አቤቱታ አቀረበ። አቤቱታውም አገራችንን የሚባርክልን አባት ይላክልን ተብሎ በቀረበ ጥያቄ መሠረት ከአባ መቃርስ ገዳም አባ ዳንኤል የሚባሉ አባት ተሹመው ተላኩልን፤ በዚያን ጊዜ የእስ ላሞች መሪ የነበረው ከሊፋ በኑቢያ በኢትዮጵያ የሚገኙትን መስጊድ አፍርስ ብለህ አቡነ ዳንኤልን ወደ ኢትዮጵያ አ ቡነ አፈወርቅን ወደ ኑቢያ ልከሃል ተብለው ፓትሪያርኩ ታሠሩ።

በዚያ ጊዜ አብዱል የሚባል እስላም አቡነ ቄርሎስ ነኝ ብሎ መጣ። ወዲያው ስለተነቃበት ተይዞ ወደ ወህኒ ቤት ወርዶ ወዲያው የእስላሞች ወዳጅ የነበሩት አቡነ ሳዊሮስ ተሹመው ተላኩ። አሳቸውም እንደመጡ መስጊድ ማሰራት ጀምረው 7 መስጊዶችን አሠርተው ወህኒ ወረዱ።

የምህራኔ ክርስቶስ ወደ እስክንድሪያ መልእክት ላኩ። አቡነ ጊዮርጊስ የሚባሉ ተሹመው ተላኩ። አቡነ ጊዮርጊስም የገንዘብ ሰው ስለሆኑ ወደ ግብፅ ተመለሱ። በዚያን ጊዜ የምህራኔ ክርስቶስ ኢትዮጵያ ከራሱዋ ልጆች ፓትሪያርክ እንድትሾም ለእስክንድርያ ሲኖዶስ አቤቱታ አቀረበ። በዚህ መሀል በአቡነ ገብርኤልና በአቡነ ሚካኤል ጠብ ተጀመረ። ኢትዮጵያ የራስዋን ልጆች እንድትሾም አብርሃም ሰሀራ የተባለ ቄስ በፍትሐ ነገስት ስላስቀመጠ ለብዙ ጊዜ ለራሱዋ እንድትሾም ተገዳ ቆይታለች።

በላሊበላ ዘመነ መንግስት የእስክንድርያ ዻዻስ አቡነ ማርቆስ ስለነበሩ በኢትዮጵያ የሚሾም ጠፍቶ መነኮሳትን አረቦች ስለፈጁ አቡነ ሚካኤል የሚባሉ ተሹመው ተላኩ። እሳቸው የንግስቲቱን ወንድም በቀናት ወርቅና ብር ሠረቀብኝ ብለው አስገደሉ። የንግስቲቱ ወንድም ነፍሰ ገዳይ ዻዻስ አንፈልግም ብለው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

አባ ሙሴ የሚባሉ መነኩሴ መጥተው አቡነ ሚካኤል ወደ አገራቸው የተመለሱበትን ሲያጠኑ ቆይተው ወደ ግብፅ ተመለሱ። አቡነ ሚካኤል በፈፀሙት የነፍሰ ግድያ ለሲኖዶስ አቅርበው አቡነ ሚካኤል በ1211 ዓ.ም ወደ ወህኒ ቤት ወረዱ።

አሁንም ኢትዮጵያ በክርስቲያን ልጆቿ ከራስዋ ልጆች እንድትሾም አቤቱታ ማቅረቧን አላቋረጠችም፤ በአፄ ይኩኑ ኣምላክም የመጣ  ዻዻስ የለም፤ አፄ ይኩኑ ኣምላክ በእስራኤል በኩል ወደ ሶሪያ ልከው ሊቀ ዻዻስ አቡነ ኢዮብ፣ አቡነ ሰላማ ብለው ላኩላቸው። በዚህን ጊዜ መንግስቱ ከላስታ ወደ ሸዋ በ1268 ዓ.ም ተዛወረ።

በአፄ አምደፅዮን ዘመነ መንግስት አቡነ ያዕቆብ ተሹመው ተላኩ። በ1487 ዓ.ም አቡነ ማርቆስንም እስላሞች ስላሰሩዋቸው በአፄ ሰይፍ አርድ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን እስላሞች በሙሉ ስላሰሩ ዻዻሱ አልተፈቱም፤ አልፈታቸውም ስላሉ አቡኑ በ1322 ዓ.ም ተፈቱ። በዚህን ጊዜ የኢየሩሳሌም ሊቀ ዻዻስ አቡነ ዮሐንስ የእስክንድርያ ሊቀ ዻዻስ አቡነ ቄርሎስ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ሲመጡ የጌታን ግማደ መስቀል ሉቃስ የሳላትን የእመቤታችን  ስዕል የጌታን አክሊለ  ሶክ ለአፄ ዳዊት አበረከቱላቸው፤ አፄ ዳዊትም የተለያዩ ስጦታዎችን ሠጥተዋቸው በ1968 ዓ.ም ወደ አገራቸው ተመለሱ።

አፄ ዘርዐያዕቆብ ከእስክንድሪያ ሲኖዶስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበራቸው በዚያን ዘመን ቁስጥንጥንያ ትንሿ እስያ ፣ ሰሜን አፍሪካ ፣አውሮዻ፣ ደቡብ ግሪክ፣እስፓኝ ፣ላይቤሪያ፣ ሩማንያ፣ ቡልጋሪያና ይጎዝላቪያ በወራሪ እስላሞች - እስላሞች እጅ ገቡ።

በሌሎች አገሮችም የደረሰው ወረራ በእግዚኣብሔር ጥበቃ ኢትዮጵያ ተርፋለች፤ ግን በኢትዮጵያ የተወለደው ግራኝ መሀመድ 15 አመት ባደረገው የጅሃድ ጦርነት በኢትዮጵያ ወገኖቹ ላይ ያልፈፀመው ግፍ የለም። እያለ ገዳማት መነኩሳት በማቃጠል የእስልምና እምነት ያልተቀበለ በሙሉ በሰይፍ ተቀልቷል።

ከ1530 ዓ.ም እስከ 1549 - ከግራኝ መሀመድ የግፍ አገዛዝ ከፖርቱጋል መንግስት በተገኘው እርዳታ ግራኝ መሀመድ ተገደለ። በ1549 ዓ.ም አፄ ገላውዲዮስ ነገሱ። እንድሪያ የሚባል የፖርቱጋል መንግስት በሰላይ በ1549 ዓ.ም የኢትዮጵያ የባህር ወደቦች እንዲያዙ መልእክት አስተላለፈ፤ በዚህ ጊዜ የፖርቱጋል መንግስት ይህን ትዕዛዝ አልተቀበሉም።

የኢትዮጵያን እምነት ለማስለወጥ ሚሲዮኖች ውስጥ ውስጡን ሲከፍሉኣቸው ቆይተው በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት በ1623 ዓ.ም አፄ ሱስንዮስ በሮማ ስርዐት ከነቤተሰቦቻቸው ተጠመቁ። የሮማ ሐይማኖትም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሀይማኖት እንዲሆን ታወጀ።

አዋጁንም የተቃወመ በአደባባይ ተጨፈጨፈ፤ ግብፃዊው አቡነ ስምኦን ንጉሡን አውግዘው በጦርነት ሞቱ። ልጃቸው አፄ ፋሲል ነገሡ። በዚያን ጊዜ ደም አፍሳሽ የነበረው የእፋኖሱ መሀንዲስ ከአገር እንዲወጣ ተደረገ። ከአገር ሲወጣም ተከትለውት ለነበሩት መነኮሳት ቅባት፣ ካራ፣ ፀጋ የሚል እምነት ጥሎ ስለሄደ ሊቃውንቱን ደም ሲያቃባ ኖሮኣል። በ1769 ዓ.ም ኢትዮጵያ በመሳፍንት እጅ ወደቀች። በዚያን ጊዜ ሚሲዮኖች አገሪቱን ለመከፋፈል አመቺ ሁኔታን ፈጠረላቸው። በየመኳንንቱና በየመሳፍንቱ ቤት እየገቡ በመሳሪያ እየደለሉ የጎጃሙን ከሸዋ፣ ጎንደሬውን፣ ከትግሬ ኦሮሞን ከአማራ በማጋጨት ደም ማፋሰስ ስራዬ ብለው ተያያዙት። በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ ዻዻስ አልነበረም።

ደጃች ውቤ አለቃ ሀብተስላሴ የተባለውን ወደ ሶሪያ ልከው የሃይማኖት አባት ይላኩልን ብለው ስላመለከቱ ወጣት መነኩሴ አቡነ ሰላማን ላኩላቸው። በ1745 ዓ.ም ደጃች ውቤ በአቡነ ሰላማ እጅ ነገሡ። አፄ ቴዎድሮስ በ1860 ዓ.ም ደጃች ውቤን ማርከው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብለው በአቡነ ሰላማ እጅ ተሾሙ።
በዚያ ጊዜ የእስክንድሪያ ሊቀነ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መጡ፤ የድድስና አቀባበል ተደረገላቸው። አቡነ ቄርሎስ ዋና የመጡበት ምክንያት አፄ ቴዎድሮስ ከቱርክ መንግስት ጋር ተጣልተው ስለነበር በሽምግልና ለማስታረቅ ተብሎ ነው።

## አፄ ቴዎድሮስና ቤተ ክህነት

አፄ ቴዎድሮስም ሁሉንም ጥያቄ በመልካም ሲቀበሉት ከቱርክ መንግስት ጋር የሀይማኖት አባት እየሆነ እንዴት ታረቀ ትላለህ፣ የቱርክ መንግስት በእየሩሳሌም የሚገኘውን የኢትዮጵያን ይዞታ - ለሌሎች ለቱርክ መንግስት ሰጥተህብናል በማለት ጳጳሱን አሰሩ።
መኳንንቶችና መሳፍንቶች አገራችን ይሠደብብናል በማለት ለቴዎድሮስ አቤቱታ አቅርበው ጳጳሱ ተፈተው ወደአገራቸው ተመለሱ። አፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ከኢትዮጵያ ለይተው የሚያዩ አገር ወዳድ መሪ ነበሩ ። ከዚያ በፊትም ከነበሩት ነገስታት ከዚያ ወዲህም ካሉት መሪዎች እንደ ቴዎድሮስ ያለ አልተፈጠረም።
በመኳንንቱ፣ በመሳፍንቱ፣ በቤተክህነቱ አድማ ከእንግሊዝ ጋር አብረው አፄ ቴዎድሮስን መቅደስ ላይ ለማንም ወራሪ እጇን አልሰጥም ብለው ሽጉጣቸውን ጠጥተው ሞቱ።
ያሁኑ ውርደት ቀድሞ ስለታያቸው ብዙ ጀግኖች ቀይ ባህር በልቷቸውም አልፏል።
ዛሬም የእሳቸውን አርማ በመከተል በቀይ ባህር ብዙ ጀግኖች ተፈጥረዋል። ከዚያም ንጉስ ተክለጊዮርጊስ በ1863 ዓ.ም ነገሡ። ከንጉሡ ዐጼ ተክለጊዮርጊስ በኋላ አፄ ዮሐንስ ስልጣንን ያዙ። በዚህን ጊዜ ሚሲዮኖችን አፄ ዮሐንስ ሰብስበው ወደ ኢትዮጵያ ለምን መጣችሁ በማለት ጥያቄ አቀረቡላቸው። መልሳቸው ወንጌል ልንሰብክ ነው፣ በአገሬ ወንጌል የሚሰብኩ ካህናት አሉኝ፤ የእስላሙን አገር ግብፅን የመንን ሱዳንን እንዴት አልፋችሁ መጣችሁ ወደ አገራችሁ ተመለሱ አሉዋቸው። ++++++
በዚያን ጊዜ አፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያ ከራስዋ እንድትሾም ለእስክድሪያ ሲኖዶስ አቤቱታ አቀረቡ፤ በዚህ መሠረት የእስክንድርያ ሲኖዶስ አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሉቃስና አቡነ ማቴዎስ የሚባሉ 3 ጳጳሳትን ሹመው ላኩላቸው።
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ከራስዋ ልጆች በንግስት ዘውዲቱ መልስ አገኘ። ለእግዚኣብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና ኢትዮጵያ በንግስት ዘውዲቱ መልስ አግኝቶ 5 ፓትርያርኮችን አፍርታለች። የመጀመሪያ አባታችን ከጣሊያን ወረራ ከ 5 አመት ስደት በኋላ አቡነ ባስሌዎስ በ1951 ዓ.ም ተሾሙ።
በ1963 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስ ተሾሙ።

## የደርግ ዘመንና ቤተ ክርስቲያን

ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ የዘውዱን ስርዐት ገርስሶ ስልጣን ሲጨብጥ ፓትርያርኩንም አፍኖ ይኑሩ ይሙቱ ሳይታወቅ ከሲኖዶስ አባል ያልነበሩትን አቡነ ተክለሀይማኖት በ1968 ዓ.ም ተሾሙ። በዚያን ጊዜ ህፃን ወጣት ሽማግሌ ሣይል አንድ ጄኔሬሽን ተጨፈጨፈ። እግዚአብሔር የለም ተባለ። የፓርቲ አባል ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ ታገዱ። ክርስትናም ልጆቻቸውን እንዳያስነሱ ታገደ።
በዚህ ስርዐት ሞት አይቀርምና አቡነ ተክለሃይማኖት ከዚህ አለም በሞት ተለዩ። አቡነ መርቆርዮስ በ1980 ዓ.ም በምትካቸው ተሾሙ። በአቡነ መርቆርዮስም ዘመን ብዙ ጦርነቶች ተካሂደዋል። አያሌ ቤተክርስቲያናት ተቃጥለዋል። ካህናት መነኮሳት ወደ ጦር ግንባር እንዲገቡ ተደርገዋል።

## ኢህአዴግና ቤተ ክርስቲያን

ከ17 አመት በኋላ ደርግ ተወግዶ ኢሕአዴግ ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ እንዳለፈው ስርዐት ኢህአዴግም በተራው አቡነ መርቆርዮስን አስወግዶ በስደት የነበሩት አቡነ ጳውሎስ ተተኩ።
አቡነ ጳዉሎስ ስልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ከምን ጊዜውም በከፋ ሁኔታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትን ከልዩ ልዩ ሚሲዮኖች ጋር ግምባር በመፍጠር የቤተክርስቲያንዋን ህልውና ማለት የሲኖዶስ ህጉን በማፍረስ ሕገወጥ የሆኑትን

ና ብቁ ያልሆኑትን አባላት በመምረጥና በመሾም በአገሪቱ እምነቱ እንዲጠፋና እንዲረክስ ቤተክርስቲያንዋ አማኝና ተከ ታይ እንዲታጣ ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ።
አቡኑ ካለው የገዢ መደብ ጋር በመወገን ዛሬ ከአስተዳደር ብልሹነት የተነሣ መሪዎች ለሚፈፅሙት የዘር፣ የጎሳ፣ የሀ ይማኖትና የቋንቋ ልዩነት በአምቻ በጋብቻ፣ በሀገር ልጅነት፣ በቤተሰብ መደራጀት፣ የጎጥ ግንባር መፍጠር፣ በቀኖና መ ፍረስ ምክንያት ትውልዱ አገሩን ለቆ በአለም የተበተነው፣ ሀይማኖቱን የተወውና የጠላው፣ ህልውናውን ለውጦ ባህሉ ን የረሳ፣ከወላጆቹ ጠፍቶ የኮበለለ ስለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።
በሰሜን አሜሪካ ፣በአውሮፓ ፣በዴንማርክ ፣በስዊድን፣ በኖርዌ ፣በግሪክ፣ በጣሊያን፣ በፈረንሣይ ፣በጀርመን ወ.ዘ.ተ. የ ተበተነው እረኛ የሌለው መንጋ ሆኖ ተበትኖ ይገኛል።
በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁጥር 11 ፣ሉቃስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 6 ፣ሕዝቅኤል ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 እስከ 19 ያለው የእግዚኣብሔር ቃል ያስረዳናል።
ከሁሉም የዘመናት አገዛዝ እምነቱ እየረከሰ ትውልዱም እምነት እልባ እንዲሆን እየተፈፀመ ያለው በአባ ጳውሎስ ፓት ርያርክ የአገዛዝ ዘመን ነው። ከዚያ በፊት የነበረው አስተዳደርም የመንግስት አባልና የስርዐቱ አጎብዳጅና አስፈፃሚ ቢ ሆኑም ቅሉ እንዳሁኑ አሣፋሪ ታሪክ አልፈፀሙም ለማለት ያስደፍራል።
የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትሪያክ አቡነ ባስሌዮስ ከ5 አመት የስደት መልስ በኋላ በንጉሱ ትዕዛዝ ተሹመዋል። የፓ ርላማ አባልም እንደነበሩ ከሣቸው ወዲያም ሁለተኛ ፓትሪያርክ አቡነ ቴዎፍሎስ እንዲሁም የፓርላማ አባል ነበሩ።
በደርግ ዘመን አገዛዝ አቡነ ተክለሀይማኖትና አቡነ መርቆርዮስም÷ በኢህአዴግም አባ ጳውሎስ የፓርላማ አባል ሆነው ሠርተዋል። እየሠሩም ይገኛሉ። በእነዚህ የአገሪቱ ፓትሪያርክ በአገሪቱ ላይ ያልተፈፀመ ግፍና በደል ያልፈሰሰ ደም የለ ም።

**የአሁኑ የአባ ጳውሎስ አስተዳደርን ከሌሎች አስከፊ ሁኔታ በአገርና በሕዝብ ላይ ተፈፅሟል የምለው፤**

1. የአገሪቱ ዳር ድንበር ለባዕድ ሲሸጥ ዝምታ የተመረጠበት፤
2. ከእናት ቅድስት ቤተክርስቲያን የተጠለሉት ወጣቶችን አሳልፈው ለሰው በላዎች የተሰጡበት፤
3. ለእውነት ቆመው ተቃውሞ ያቀረቡና የጠየቁትን በጨለማ ተይዘው በስርዐቱ እንዲደበደቡ፣ እንዲገደሉ፣ እንዲታሠሩ የተደረገበትና አንድም ተቃውሞ እንዳያቀርቡ የታገደበት፤

በአገር ውስጥ ቀርቶ በውጭ አገር ካድሬዎቻውን በመላክ በውጭ ያለው የሲኖዶስ ቤተክርስቲያን እንዲጠፋና እንዲረክ ስ፣ሠላም እንዲያጣ በማድረግ እምነቱን እያራከሱ ያሉበት ወቅት ነው።
ለዚህ ሁሉ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አለም በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች፣ ቤተክርስቲያናት ፣አድባራት ፣ገዳማት ሁሉ ለሚፈፀመው ጥፋቶች ሁሉ ከታሪክ ተጠያቂነት አያመልጡም።

አባ ጳውሎስ በስመ ፓትሪያርክ ÷ ነፍሳዊ ህይወትን ወደጎን በመተው ለስጋዊ ሕይወታቸው በማደር ዛሬ እንደፓትሪያር ክም እንደ ምድራዊም ኑሮ ከእምነቱ ውጭ በእግዚኣብሔር መሣሪያነትና ሐያልነት ባለማመን፣ መሣሪያ- ሽጉጥ ታጥቀ ው ምእመናኑንና ከስር ያሉ አስተዳዳሪዎችን በማስፈራራት ከስርዐቱ ጋር ወግነው እምነቱን እያራከሱ ይገኛሉ።
ዛሬ በአገራችን እንደምናየው በዚህ ፓትሪያርክ መሠሪ ደባ ምእመናኑ ሆኑ ጳጳሳቱ/ገዳማቱ በአደገኛ ሁኔታ ላይ ወድቀው መገኘታቸው የአደባባይ ምስጥር ነው።

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት አንድ ፓትሪያርክ በስሩ ያሉትን ምእመናን እንደልጆቹ አይቶ ልጆቹ ፊታቸውን ወደእግ ዚኣብሔር መልሰው የእግዚኣብሔር ተገዥና ተከታይ እንዲሆኑ እምነቱ በሁሉም ተከታዮች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ የሀይማኖትና የተቀደሰች አገር እንድትሆን መደረግ ሲገባ፤ እሳቸው ግን ከማንም ከምንም ስልጣን ሳይሰጣቸው ከስደት አገር ወያኔ ምድራዊ ስልጣን ለስርዐቱ አገልጋይነት የሚቀረቀሩትን አድነው በመንግስት ደህንነት እያስያዙ አደጋ እያደ ረሱባቸውና ምእመናኑ ፀጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ የክህደት ተግባር በአገርም በሕዝብም ላይ እየፈፀሙ ይገኛሉ።

## ስለዚህ ውድ የአገሬ ሕዝብ ሆይ፤

የምድራዊ ኑሮ አላፊና ጊዜያዊ መኖሪያ እንጂ የዘለአለም ቤታችን እንዳልሆነ የማይረዳ የለም። አባ ዻውሎስ ግን የስር ዐቱ አጎብዳጅና አስፈፃሚ በመሆን እሳቸው የገቡበት ምድራዊ ሕይወት ተታለን ፈጣሪን እንድንረሳ፣ እንዳናመልክ፣ ከፍ ተኛ ደባ እየተፈፀመብን ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥ፣ በውጭ አገር የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይና ሀገር ወዳ ድ የሆንነው መላው የአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች በሙሉ ለማስተላለፍ የምፈልገው÷
ሁላችንም የዚህ የእናት ቤተክርስቲያናችን ውድቀት አውቀንም ሆነ ባለማወቅ የጥፋቱ ተባባሪ ሆነን እንገኛለን። የውጭ የአገር ቤት ሲኖዶስ፣ የዻውሎስ ደጋፊ ፣የመርቆሪዮስ
ደጋፊ በመባባል አገራችንንና እምነቷንም ጭምር እያጠፋን እንገኛለን።

## የስርዐቱ ደጋፊና ተጠቃሚ የሆንከው ወገኔ ሆይ!

ወደፊት በአገርና በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል ማክሸፍ የተተኪው ትውልድ እጣ ፈንታ ነው። የአገሪቱ የነገ ተረካቢ ተተኪው ትውልድ መሆንክንም አትዘንጋ፤ ላንተና ለልጆችህም ጭምር ጥቁር ነጥብ እየጣልን መሆኑን በጥሞና እንመልከተው።
በፅሁፌ ማጠቃለያ ላይ ከላይ እንደተመለከተው ማንም አገሬ ናት፤ አገር አለን፤ እምነትም አለኝ የሚል ዜጋ ሁሉ ይህ በአገርና በሕዝብ ላይ የተጋረደው ጥቁር ዣንጥላ በአገሪቱ የሕግ የበላይነት ጠፍቶ ዜጎች በአደባባይ በጥይት እየተደበ ደቡ፤ በእስራት፣በበግርፋት እየተሰቃዩና ይህንም ቅድስት ቤተክርስቲያናችንም ጥላና መከታ እንዲሆናቸው የተጠለሉት ን አሳልፎ በሚሰጥበት አገርና፣ አገር እንደዳቦ ተቆርሶ ለባእድ እየተሠጠ እያለ ሰምተን እንዳልሰማን ሆነን እምነትና አገ ር አልባ መሆን የሌለብን ስለሆነና ይህንንም በዝምታ ማየቱ ታሪኳንም እምነቷንም ማበላሸትና ማጥፋት በመሆኑ ልንከላ ከል ይገባል።

ትናንት ለዚህ ለአገር፣ ለእምነት ለሰላምና ለዲሞክራሲ መስፈን ሲሉ በጥይት በአደባባይ የተደበደቡትን በአሁኑ ጊዜ በዚህ በግፈኛው ስርዐት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በእስር ቤት እየማቀቁ ያሉትን እንደነ ብርቱካን ሚደቅሣ፣ የሌሎችን ም የትግል አርማ አንግበን አንስተን እነሱ የሞቱበትንና እየተሰቃዩ ያሉበትን አላማ ከግብ ለማድረስ ሁላችንም - ሆ - ብለን ልንነሣሣ ይገባል።
ያለበለዚያ አገራችን የምንላት በወያኔ ተቆራርሳ ያለችው ነገ ጭራሹንም አገር አልባና እምነት አልባ ሆነን ለልጆቻችን ም አገር አልባ እንዲሆኑ መዳረግ የታሪክ ተወቃሽነት የሚያስከትልብን ስለሆነ ***"ምት አይቀርም ስም አይቀበርም"*** እንደተባለው የአበው ተረት በመሃከላችን በወያኔ የተረጨብንን መርዝና የእርስ በርስ ያለመተማመን ጥላችንን አስወግደ ን - ሆ- ብለን በአንድነት በመነሣሣት፤ በመሃከላችን ያለውን ልዩነት ተቀራርበን በመወያየት በመነጋገር ልዩነቶቻችንን አስወግደን እንደአቅማችንና እንደችሎታችን በመደጋገፍ "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" ነውና በአንድነት ተያይዘን እጅ ለእጅ እንነሣሣ በማለት ጥሪዬን አቀርባለሁ።

1ኛ/ እስከመቼ ድረስ ቤተክርስቲያናችን ከመንግስት ተፅዕኖ ሁና የእምነት አገልግሎቷን መስጠት ይኖርባታል?
2ኛ/ የሃይማኖት አባቶች ከመንፈሳዊ ልጆቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ለምን ተሳናቸው?
3ኛ/ ቤተክርስቲያናችን በቀኖና መፍረስ ምክንያት፤
ሀ/ የጎሠኝነት ቡድን መፈላለጊያና ዋሻ እየሆነች መሄድ፤
ለ/ ለፖለቲካ ፓርቲ አጋርነት ማንፀባረቂያና የማይፈለጉ ካህናትን መመንጠሪያ መድረክ መሆን
ሐ/ ሃይማኖትንና የፖለቲካ አመለካከትን በቅጡ ለይቶ ካለማወቅ የተነሣ፤ በከፍተኛ ባለማዕረግ ዻዻሳት ካህናት ብሎም በምዕመናንም በተዋረድ አሉታዊ ተፅዕኖ በማምጣቱ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተክርስቲያን የመንግሥት መለወጥ በሚከሰትበ ት ወቅት፤ የዚሁ ሰለባ እየሆነች ከመዳበር ይልቅ እያደር እየቀጨጨች መሄዷ፤

**ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በፅሞና መርምሮ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ያሉ የሚመለከታቸው አባቶች ውል-ያለው ሥራ ከወዲሁ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።**

***በመጨረሻም  የኛ አባቶች ከበርማ መነኮሳት ምን ይማራሉ? ሃይማኖት የክርስቶስ መገናኛ ድልድይ እንጂ የአሳይለም መ ጠየቂያ መሆን አልነበረበትም!***

**ልዑል እግዚኣብሔር አገራችን  ከጥፋት ይጠብቅልን**
**ለነፃነታቸው  ሲሉ የተሠውት በሙሉ ነፍሳቸውን ይማርልን**
**ታስረው የሚገኙትንም ፅናቱን እንዲሁም እግዚአብሔር እንዲጎበኛቸው**

**ሐምሌ** 4 **ቀን** 2002 **ዓ.ም**
**የማነብርሃን ጥበቡ/ከጀርመን አገር**

Email: yematibeb2010@yahoo.de